# ክራዮቴራፒ (Cryotherapy)

**ክራዮቴራፒ (Cryotherapy) ቀጥተኛ ትርጉቻሙ በዝቅተኛ ሙቀት (በበረዶ) የሚደረግ ህክምና ("Treatment using low temperature") ማለት ሲሆን፤ በቆዳ ላይ የሚወጡየተለያዩ አይነት በሽታዎችን ለማከም ያገለግላል:: በዝህ የመረጃ ጽሁፍ ክራዮቴራፒ ምን እንደሆነ፣ አገልግሎቶቹ ና የጎንዮሽ ችግሮቹ ይዳሰሳሉ::**




የፈሳሽ ናይትሮጂን መያዣ ሲሊንደር



የጥጥ መኪያ




የመርጫ መሳርያ (Cryo-gun)

## ክራዮቴራፒ ምንድን ነዉ?

- **ክራዮቴራፒ** (Cryotherapy) በበሽታ የተጠቁ ህብረ-ህዋሳትን ለዝቅተኛ ሙቀት መጠን በማጋለጥ (በበረዶ በመምታት) የማስወገድ የህክምና ዘዴ ነዉ:: የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችን በማከም ከፍተኛ የፈዉስ ምጣኔ የተመዘገበበት ዘዴ ነዉ::

- **ክራዮጂንስ** (Cryogens) በክራዮቴራፒ የህክምና ስልት ዉስጥ የሰዉነታችንን ህብረ-ህዋሳት ወደ ነጥበ-ብርደት ለማድረስ የምያገለግሉ መድሐኒቶች ክራዮጂንስ ይባላሉ:: ክራዮጂንስ የተለያየ ነቁጠ-ቅዜት ስላላቸዉ የተለያዩ የበሽታ አይነቶችን ለማከም ያገለግላሉ::

- **ፈሳሽ ናይትሮጂን** (Liquid Nitrogen)
  - ናይትሮጂን በከባቢ 78% ያህል ይይዛል
  - በኔጌቲቭ 196°c. የሙቀት ደረጃ ወደ ፈሳሽነት ይቀየራል
  - የተለያዩ የቆዳ ችግሮችን ለማከም ያገለግላል

## የክራዮቴራፒ ህክምና አሰጣጥ

- ፈሳሽ ናይትሮጂኑን በቆዳ ላይ ቁስለት ላይ ለማድረግ የመርጫ መሳርያ (Cryo-gun) ወይም የጥጥ መኪያ በመጠቀም ይከናወናል
- በበረዶ የተመታዉ ቦታ ላይ መጠነኛ ህመም ቢፈጠርም ማደንዘዣ መጠቀም አያስፈልግም
- በቆዳ ላይ የሚደረገዉ ፈሳሽ ናይትሮጂን መጠን የሚመጠነዉ በቁስለቱ ስፋት ና ዉፍረት መሰረት ነዉ::
- ቁስለቱ በበረዶ ከተመታ ቦኃላ መልኩ ወደ ነጭ ይቀየርና ከ2-3 ደቂቃ ቦኃላ ወደ ቀድሞ መልኩ ይመለሳል::

- ፈሳሽ ናይትሮጂን ከተደረገ ከ2/3 ቀን ቦኃላ ቅርፊት መበጀት ይጀምራል፤ ቅርፊቱም እስከ 3 ሳምንት በሚሆን ጊዜ ዉስጥ በራሱ ጊዜ ይወድቃል::
- እንደህመምዎት አይነት ተደጋጋሚ ህክምና ልያስፈልግዎት ስለሚችል ቀጠሮዎትን አክብረዉ ህክምናዎን ይከታተሉ::



















## የክራዮቴራፒ ህክምና በኃላ አስፈላጊ የሆኑ ጥንቃቄዎች

**በበረዶ ለተመታዉ ቆዳዎ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች (እንክብካቤዎች) ማድረግ ይመከራል፡-**

- ቆዳዎ ከደረቀ (ድርቀት ካመጣ) ቫዝሊን መቀባት
- እርጥበት ካመጣ በንፁህ ፎጣ ጫንጫን በማድረግ ማድረቅ
- ቅርፊት ሰንኮፉን በራሱ ጊዜ ሳይወድቅ መላጥ ጠባሳ የመፈጠር እድሉን ይጨምራል ለዚህ ቅርፊቱን ፈፅሞ አይላጡት
- በበረዶ የተመታዉ የሰዉነት ክፍልዎ ለግጭት (ፍትግያ) የተጋለጠ ካልሆነ በፕላስተር ወይም በጨርቅ መጠቅለል አይመከርም

## በክራዮቴራፒ የሚታከሙ በሽታዎች

- ኪንታሮት (Viral Warts) (ስዕል-ሀ ይመልከቱ)
- Molluscum Contagiosum (ስዕል-ለ ይመልከቱ)
- የተጋነነ ጠባሳ (ኬሎይድ) (ስዕል-ሐ ይመልከቱ)
- Seborrheic Keratosis (ስዕል-መ ይመልከቱ)
- Actinic Keratoses (ስዕል-ሠ ይመልከቱ)

## የክራዮቴራፒ ህክምና የጎንዮሽ ችግሮች

### ወድያዉኑ የሚከሰቱ ችግሮች (Immediate Side effects):

- **ህመም:** ከበድ ያለ ህመም ከተሰማዎ የህመም ማስታገሻ መድሐኒቶችን መጠቀም ይችላሉ፡፡
- **እብጠት:** በበረዶ የተመታዉ አካባቢ እብጠት ና ቅላት ሊከሰት ይችላል፤ በተጨማሪም ዉሃ የመሰለ ፈሳሽ/ ደም ሊመነጭ ይችላል፤ አያሳስብዎ እብጠቱ በሳምንት ጊዜ ዉስጥ ይስተካከላል፡፡
- **ፈሳሽ መቋጠር:** ይህ ብዙ ሰዉ ላይ የሚከሰት የተለመደ ችግር ሲሆን በቀናት ጊዜ ዉስጥ ቅርፊት ሰንኮፍ መሰራት ሲጀምር ይጠፋል፡፡ ስለዚህ፡-
    - ፈሳሹን መነካካት/ ማፍረጥ አያስፈልግም
    - ምቾት የሚነሳ ህመም ካለዉ ሀኪምዎን ያማክሩ
- **የባክቴሪያ እንፌክሺን:** እየጨመረ የሚመጣ ህመም/ መግል የመያዝ ምልክቶች ካዩ ሀኪምዎን ያማክሩ

### የኋላኋላ የሚከሰቱ ችግሮች (Subsequent Side effects):

- **ጠባሳ:** ቆዳችን በጥልቀት በበረዶ ሲመታ ይከሰታል፡፡
- **የተጋነነ ጠባሳ (Keloid):** በተፈጥሮ ለችግሩ ተጋላጭ በሆኑ ሰዎች ላይ ይከሰታል፡፡
- **የቆዳ ከለር (መልክ) መቀየር:** የቆዳ መንጣት ወይም መጥቆር በበረዶ የተመታዉ ቦታ ላይና ዙርያዉ ላይ ይከሰታል፤ በወራት ዉስጥ ወደቀድሞ መልክ ይመለሳል፡፡
- **የመደንዘዝ ስሜት:** ሱፐርፊሻል ነርቮች በበረዶ ሲመቱ ይህ ችግር ያጋጥማል፤ አያስቡ ችግሩ ቋሚ አይደለም፤ በጊዜ ሂደት ይስተካከላል፡፡





















ዶ/ር ዮሐንስ ኃ/ሚካኤል (የቆዳ ና አባለዘር በሽታዎች ስፔሻሊስት) (ስልክ 0911 98 58 17